



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ


የ2015 በጀት ዓመት
የተደገፈ በጀት

ጥራዝ II

የፕሮግራም በጀት ዝርዝር መግለጫ

ግንቦት 25/2014


ሌሎች
172,673.1
50.03%
አስተዳደርና
ጠቅላላ
አገልግሎት
111,693.4
32.36%
የመደበኛ
ወጪ
/በሚሊዮን ብር
ማህበራዊ
53,754.7
15.58%
ኢኮኖሚ
6,995.2
2.03%


ሌሎች
6,513.5
2.99%
አስተዳደርና
ጠቅላላ
አገልግሎት
29,644.6
13.6%
የካፒታል
ወጪ
/በሚሊዮን ብር
ማህበራዊ
48,691.0
22.3%
ኢኮኖሚ
133,263.8
61.1%

ማውጫ **ገጽ**

መ ግ ቢ ያ 1

የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ 2

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት 7

የፌደራል ዋና ኦዲተር 10

የፌዴሬሽን ም/ቤት 14

የቤተ መንግስት አስተዳደር 18

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት 21

የሰላም ሚኒስቴር 24

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን 28

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር 35

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን 39

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም 44

የፍትህ ሚኒስቴር 47

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች 52

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት 56

የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት 60

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር 63

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር 69

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 72

የገንዘብ ሚኒስቴር 75

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት 80

የመገናኛ ብዙሓን ባለስልጣን 84

የመንግስት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት 87

የገቢዎች ሚኒስቴር 90

የጉምሩክ ኮሚሽን 94

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር 97

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር 102

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ 107

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን 110

የኢኮኖሚ ዘርፍ 115

የግብርና ሚኒስቴር 116

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት 121

የኢትዮጵያ ደን ልማት 127

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን 130

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን **134**

የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት 138

የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት 141

የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት 145

የውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር 149

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር 152

የማዕድን ሚኒስቴር 155

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር 158

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር 166

የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር 171

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት 178

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር 182

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር **190**

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን 199
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን 203
ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት 207
የማህበራዊ ዘርፍ 218
የትምህርት ሚኒስቴር 219
የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት 223
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 226
ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ 230
ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ 234
መቀሌ ዩኒቨርሲቲ 238
ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ 242
ጅማ ዩኒቨርሲቲ 247
አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ 251
ጎንደር ዩኒቨርሲቲ 255
የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ 259
የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ 263
ቦረና ዩኒቨርሲቲ 267
የአርሲ ዩኒቨርሲቲ 270
የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ 273
የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ 276
የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ 279
የቀብሪደሀር ዩኒቨርሲቲ 282
የጂንካ ዩኒቨርሲቲ 286
የራያ ዩኒቨርሲቲ 289
የመቅደላ ዩኒቨርሲቲ 292

የደባርቅ ዩኒቨርሲቲ 295
የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ 298
የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ 301
የወራቤ ዩኒቨርሲቲ 304
ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ 307
አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ 311
ዲላ ዩኒቨርሲቲ 314
ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ 318
ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ 322
ወሎ ዩኒቨርሲቲ 326
ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 331
ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 335
ወለጋ ዩኒቨርሲቲ 338
አክሱም ዩኒቨርሲቲ 342
መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ 346
ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ 349
ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ 353
ሰመራ ዩኒቨርሲቲ 357
አምቦ ዩኒቨርሲቲ 361
የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ 365
የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ 368
የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ 371
የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ 374
የደብረ-ታቦር ዩኒቨርሲቲ 377
የመቱ ዩኒቨርሲቲ 380

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ 383

የቡሌ-ሆራ ዩኒቨርሲቲ 386

አሶሳ ዩኒቨርሲቲ 390

የቱሪዝም ሚንስቴር 393

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር 396

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት 406

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር 409

የጤና ሚኒስቴር 414

የኢትዮጲያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲዩት 419

የኢትዮጵያ የምግብ እና መድሃኒት ባለሥልጣን 422

ኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት 426

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል እና ሚሊኒየም የሕክምና ኮሌጅ 429

የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን 432

መደበኛ - ከመንግስት ግምጃ ቤት እና ከመ/ቤቱ ገቢ የተሰጠ ጣሪያ፣ የተጠየቀና
የተደገፈ ማወዳደሪያ 440

ካፒታል - ከመንግስት ግምጃ ቤት እና ከመ/ቤቱ ገቢ የተሰጠ ጣሪያ፣ የተጠየቀና
የተደገፈ ማወዳደሪያ 447

ጠቅላላ - ከመንግስት ግምጃ ቤት እና ከመ/ቤቱ ገቢ የተሰጠ ጣሪያ፣ የተጠየቀና
የተደገፈ ማወዳደሪያ 453

የካፒታል ወጪ የተጠየቀና የተደገፈ በጀት በመንግስት መ/ቤት ወይም በሥራ
ክፍል እና በፋይናንስ ምንጭ ማወዳደሪያ 462

ካፒታል በጀት በለጋሽና በንዑስ ዘርፍ 553

ካፒታል በጀት በአበዳሪና በንዑስ ዘርፍ 555

መ ግ ቢ ያ

የአራተኛው ዙር የ2013-2015 የፕሮግራም በጀት አካል የሆነው የ2015 በጀት ዓመት ሶስተኛ ዓመት በመሆኑ የ2014 የግማሽ ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ከግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቶ ቀርቧል። የ2015 በጀት ዓመት የፌደራል መንግሥት በጀት በፕሮግራም በጀት አሠራር ሥርዓት መሠረት ባለበጀት መ/ቤቶች በተዋቀሩበት የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ፣ የኢኮኖሚ ዘርፍ፣ የማኅበራዊ ዘርፍ እንዲሁም ሌሎች በሚለው ሥር የዕዳ ክፍያ፣ የመጠባበቂያ በጀት እና የመሳሰሉት ቀርቧል። ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ አስፈጻሚ መ/ቤት ያቀረበውን የበጀት ጥያቄ በመገምገም በፕሮግራም ደረጃ በመደበኛና ካፒታል ወጪ በመለየት የበጀት ድጋፉ ተጠቃሎ ተመልክቷል።

ይህ የበጀት ድጋፍ የመንግሥትን የትኩረት አቅጣጫ መሠረት ያደረገና ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር የበጀት ስሚ በማካሄድ የተዘጋጀ ነው።

በዚህ የበጀት ሰነድ የእያንዳንዱ ባለበጀት መ/ቤት ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ከመንግስት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር፣ የዓላማዎችና ፕሮግራሞች መግለጫ እና የ2015 የመደበኛና ካፒታል ወጪ በፕሮግራም እንዲሁም ውጤቶችን፣ አመልካቾችና ዓመታዊ ግቦችን በማካተት የፕሮግራም በጀት ማጠቃለያ በዝርዝር ቀርቧል።

የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ

በአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ ሥር ለሚገኙ 64 ባለበጀት መ/ቤቶች ለ2015 በጀት ዓመት በዕቅድ ለያዟቸው ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የቀረበው የበጀት ጥያቄ ለመደበኛ ወጪ ብር 129,534.9 ሚሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ደግሞ ብር 36,876.82 ሚሊዮን በአጠቃላይ ብር 141,337.98 ሚሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 140,746.67 ሚሊዮን ከመንግሥት ግምጃ ቤት የተጠየቀ ነው።

የቀረበውን የበጀት ጥያቄ በዝርዝር በመገምገም ለመደበኛ ወጪ ብር 111,102.07 ሚሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ብር 29,644.61 ሚሊዮን፣ በአጠቃላይ ብር 141,337.98 ሚሊዮን ተደግፏል። ከተደገፈው በጀት ውስጥ ብር 140,746.67 ሚሊዮን ከመንግሥት ግምጃ ቤት፣ ብር 591.31 ሚሊዮን ከመስሪያ ቤት ገቢ ነው። ከተደገፈው በጀት ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ገንዘብ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን እንደ ቅደም ተከተላቸው ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል። ለ2015 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ለዘርፉ የተደገፈው በጀት ለ2014 ከጸደቀው በጀት ጋር ሲነፃጸር የብር 81,667.00 ሚሊዮን ወይም 136.9 በመቶ ብልጫ አሳይቷል።

በዚህ ዘርፍ ለሚገኙ መ/ቤቶች ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች፣ አመልካቾች፣ ግቦች እና ለእያንዳንዱ ፕሮግራም ለ2015 የተደገፈ በጀት እንደሚከተለው ቀርቧል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ልማት፣ አንድነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ የውክልና፣ የሕግ ማውጣት እና የክትትልና ቁጥጥር ሕገ-መንግስታዊ ኃላፊነቱን በብቃት በመወጣት የህዝብ ድምፅ መሆን፤

1.2 ራዕይ

ህገ-መንግስታዊ ኃላፊነቱን የሚወጣ የተለወጠ፣ ነፃ እና የሕዝቦችን ፍላጎት የሚወክል ውጤታማና ምላሽ ሰጭ ምክር ቤት መሆን፤

2. ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተጀመረውን ልማት የሚያስቀጥሉና የህዝቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ጥናታዊ ግኝትን መሰረት ያደረጉ ህጎችንና ፖሊሲዎችን በማውጣት፣ የሚመደበው የመንግስት ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ለማስፈን የሚያስችል ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ስኬታማነት አንጻር ሲታይ ዕቅዱ ውጤታማ እንዲሆን ሊጫወት የሚገባው ቁልፍ ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይታመናል።

በምክር ቤቱ ውሳኔዎች ላይ ህዝቡ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ለዴሞክራሲ መጎልበት የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችል ዘንድ ምክር ቤቱን ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በስፋት እንዲሳተፉ የማድረጉ ሥራም ለ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ስኬት ወሳኝ ተግባር ነው።

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5 ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን ለእነዚህ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 352.29 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 59.69 ሚሊዮን በድምሩ ብር 411.97 ሚሊዮን ተደግፏል።

4. የመ/ቤቱ ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች እና ግቦች

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1 የም/ቤቱ ጽ/ቤት መደበኛ ድጋፎችና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን በለውጥና መልካም አስተዳደር መርህ መሠረት በመተግበር አሁን ካለበት 87% ወደ 90% ማሳደግ	**ፕሮግራም 1፡ የሥራ አመራርና አስተዳደር** ይህ ፕሮግራም በዋነኛነት ምክር ቤቱ ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት ይችል ዘንድ መደበኛ ድጋፍና አስተዳደራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ የተቋቋመው የምክር ቤቱ ጽ/ቤት የሚያከናውናቸውን ተግባራት በማካተት የተቀረጸ ነው።	➢ የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች ➢ የተገነባ ህንፃ	በመቶኛ በመቶኛ	100 100
ዓላማ 2 በሕጎች፣በፖሊሲዎች፣በስትራቴጂዎች፣ በፕሮግራሞች እና በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ የሚደረገውን ክትትልና ቁጥጥር እና የሕዝብ ውክልናን መድረክ 100% ማድረስ	**ፕሮግራም 2፡ የክትትል፣ቁጥጥር እና የህዝብ ውክልና** በዚህ ፕሮግራም ሥር የዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችንና ጥቆማዎችን መመርመር እንዲሁም በህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች አፈጻጸም ላይ በመስክ ምልከታ የታገዘ ክትትልና ቁጥጥር ማካሄድና ከመራጩ ሕዝብ ጋር ግንኙነት ይደረጋል።	➢ የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር ➢ የዳበረ የህዝብ ውክልና	በመቶኛ በመቶኛ	100 100
ዓላማ 3 ምክር ቤቱን ለህዝብ ተደራሽነት አሁን ካለበት ከ1,000,000 ወደ 1,500,000 ህዝብ ማድረስ እና ፓርላሜንታዊ ዲፕሎማሲን 100% በመፈፀም የምክር ቤቱን ገፅታ መገንባት	**ፕሮግራም 3፡ የምክር ቤት ተደራሽነትና የገጽታ ግንባታ** የምክር ቤት ተደራሽነትና የገጽታ ግንባታ ፕሮግራም ምክር ቤቱን ለህዝብ ተደራሽ በማድረግና ህዝቡ በም/ቤቱ ጉዳዮች ላይ የሚኖረውን ተሳትፎ በማጎልበት እና ፓርላሜንታዊ ዲፕሎማሲን በማጎልበት የአገራችና የምክር ቤቱን ገጽታ ከመገንባት አንጻር የሚከናወኑ ተግባራትን የሚመለከቱ ወሳኝ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ የተቀረፀ ፕሮግራም ነው።	➢ የጎለበተ የህዝብ ተሳትፎ ➢ የተጠናከረ ፓርላሜንታዊ ዲፕሎማሲ	በመቶኛ በመቶኛ	100 100

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 4 ሰላም ፣ ልማት ፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችሉ ሕጐች ማጽደቅን 100% ማድረስ	**ፕሮግራም 4፡ የሕግ አወጣጥ** ይህ ፕሮግራም የምክር ቤቱ አንዱ ተግባር የሆነውን ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነት የሚመለከት ሲሆን አወቃቀሩም በሰብአዊ አገልግሎት በኩል በክትትልና ቁጥጥሩ ዘርፍ ያልተካተቱ የምክር ቤት አባላትን በማካተት፣ ዘርፉን በተለይም የህትመት ክፍሉን በዘመናዊ የኮንፈረንስ፣ የህትመት እና የዶኩመንቴሽን መሣሪያዎች የማደራጀት፣ ለም/ቤቱ በቀረበ የህግ ረቂቅ ላይ ሙያዊ አስተያየት የመስጠት፣ፓርላሜንታዊ ጥናት የማድረግና ሙያዊ ድጋፍ የመስጠት፣የቃለጉባኤ፣ የአፍታ ትርጉምና የድምጽ ቀረጻ አገልግሎት የመስጠት፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት የማስፋፋት ስራዎችን፣ እንደዚሁም የምክር ቤቱን ቤተመጻህፍት በመጻህፍትና በወቅታዊ የህትመት ውጤቶች የማጠናከር ስራዎች በማከናወን የሕግ አወጣጥ ሂደቱን የማሳለጥ ዋና ዋና ተግባራትን መሠረት አድርጎ የተቀረፀ ነው።	➢ የወጡ ሕጎች	በመቶኛ	100
ዓላማ 5 የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ከሁሉም ኘሮግራሞች እና ተግባራት ጋር አካቶ በመተግበር በኩል አሁን ያለውን 85% ወደ 87% ማድረስ	**ፕሮግራም 5፡ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች** ይህ ፕሮግራም በሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠውን የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ፕሮግራምን የሚመለከት በመሆኑ የም/ቤቱ ጽ/ቤት እንደ አንድ ፈጻሚ በሴቶችና ህፃናት፣ በኤች አይቪና ኤድስ፣ በአካባቢ ጥበቃና በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዙሪያ መወጣት የሚገባውን ተግባር ለማከናወን እንዲችል የተቀረፀ ፕሮግራም ነው።	➢ በባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ላይ የተፈጠረ ግንዛቤ	በመቶኛ	100

5. የ2015 ለመስሪያ ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

/በሺህ ብር/

የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	ካፒታል					መደበኛ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግ/ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግ/ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10	11=7+10
111	የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት	**59,689**				**59,689**	**352,285.80**			**411,974.80**
1	ሥራ አመራርና አስተዳደር	59,689				59,689	105,939.79			105,939.79
2	የክትትል፣ ቁጥጥር እና የህዝብ ውክልና						166,362.13			166,362.13
3	የምክር ቤት ተደራሽነትና የገጽታ ግንባታ						31,407.75			31,407.75
4	የህግ አወጣጥ						45,790.235			45,790.235
5	የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች						2,785.894			2,785.894

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህገመንግሥታዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ በመደገፍ የህዝቦችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

1.2 ራዕይ

የህግ የበላይነት የተከበረባት ዘላቂ ልማት የሰፈነባትና የህዝቡ ተጠቃሚነት ያደገባት ሀገር እንድትሆን ለማድረግ የድጋፍ አገልግሎቱን ጥራትና ውጤታማነት ማሻሻል፡፡

2. ከ10 **ዓመቱ መሪ የልማት** ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

መንግስት መንግስት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት፣ ሰላምን ለማስፈን፣ ልማትን ለማረጋገጥ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ዕቅዶችን በመንደፍ እና በማውጣት በተግባር ላይ እያዋለ ይገኛል:: የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሀገራዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሠረት በማድረግ በየሴክተር መ/ቤቶቹ የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተያዘው ዕቅድ እና የአፈጻጸም አቅጣጫ መሠረት በየዓመቱ ተሸንሽኖ መታቀዳቸውን መተግበራቸውን በቀጣይነት መከታተል እና በመደገፍ የማስተካከያ አቅጣጫዎችን የመስጠት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

በዚህም ጽ/ቤቱ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የሎጅስቲክስና የሴክሬታሪያት ድጋፍ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በመስጠት መንግስት የጀመረውን ለውጥ በማስቀጠል ህዝቡ በላቀ ደረጃ የሚጠቀምበት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥና በአገር አቀፍ ደረጃ የተነደፉ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና እቅዶች በአግባቡ እንዲሳኩና የዲሞክራሲ ስርዓት በጠንካራ መሰረት ላይ ለመገንባት ለሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ግንባር ቀደም ሆኖ በመፈፀም ለአገራዊ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ ዕቅድ ተግባራዊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል::

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

ለሚኒስቴር ፅ/ቤቱ 2015 በጀት ዓመት 3 ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን ለእነዚህ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 260.4 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 150.0 ሚሊዮን በድምሩ ብር 410.4 ሚሊዮን ተደግፏል፡፡

4. የመ/ቤቱ ዓላማዎች፣ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች እና ግቦች

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች /የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1፡ 100% ጥራት ያለዉ የድጋፍ አገልግሎት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለምክትል ጠ/ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ም/ቤት መስጠት	**ኘሮግራም 1፡ የሥራ አመራርና አስተዳደር** በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ለሚገኙ የተለያዩ የሥራ ዘርፎችና የሥራ ሂደቶች የዕቅድና ለውጥ አመራር፣ የሰዉ ሀብት ስራ አመራር፣ የፋይናንስ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር፣ የጋራ አገልግሎት፣ ለተሸከርካሪ ስምርትና ጥገና፣ የአዲት፣ አገልግሎት፣ የባለብዙ ዘርፍ፣ የፕሮቶኮል እና የሚኒስትሮችና ሚኒስትር ዴኤታዎች አገልግሎቶች የሚሰጥበት ፕሮግራም ነዉ፡፡	• የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች		
ዓላማ 2፡ ከ2013-15 የተነደፉትን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎች እና እቅዶች ዉጤታማ ለማድረግ ጥራት ባለዉ እና በተሟላ መልኩ መተግበራቸዉን **100%** ማረጋገጥ	**ኘሮግራም 2፡ እቅድ ዉጤታማነት ክትትልና ድጋፍ** የአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መንግስት በነደፈዉ አቅጣጫ መሰረት ተግባራዊ መሆናቸዉን በመከታተል እና በመደገፍ ዉጤታማ እንዲሆኑ የሚደረግበት ፕሮግራም ነዉ፡፡	• ተግባራዊ የተደረገ የመንግስት ፖሊሲና ዕቅድ • ጥራቱንና ወቅቱን ጠብቆ ለበላይ አካል የቀረበ መረጃ	% %	100 100
ዓላማ 3፡ ከ2013-2015 **100%** ጥራት ያለዉ የህግ ጉዳዮች የካቢኔ ሴክሬታሪያት የሹመት ሽልማትና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ መስጠት	**ኘሮግራም 3፡ የካቢኔ ጉዳዮች፡ አስተዳደራዊ ጉዳዮች እና ሹመት ሽልማት** ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የተቀናጀ የሕግና የሴክሬታሪያት ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጥበት እንዲሁም የተሿሚዎችን ጥቅማጥቅም በሕጉ መሠረት እንዲሟላ ማድረግ፣ አስተያየትና የውሣኔ ሃሳብ ማቅረብ፣ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና ቅሬታዎችን መርምሮ ለውሣኔ የማቅረብ ድጋፍ የሚደረግበት ፕሮግራም ነዉ፡፡	• ደረጃቸውን ጠብቀው የተዘጋጁ ሕጎችና የህግ አስተያየቶች • ወቅቱንና ደረጃቸውን ጠብቀው የተሰጡ የካቢኔ ሴክሬታሪያት አገልግሎት • ጥቅማ ጥቅማቸው የተጠበቀላቸው ተሿሚዎች • አስተያየትና የውሣኔ ኃሣብ የቀረበባቸው አቤቱታዎች	% % % %	100 100 100 100

6. የ2015 ለመ/ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	የ ካ ፒ ታ ል ወጪ					የ መ ደ በ ኛ ወ ጪ			ጠቅላላ ድመር
		ከመንግሥት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግሥት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10	11=7+10
112	የጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት	150,000.00				150,000.00	260,464.82		260,464.82	410,464.82
1	የሥራ አመራርና አስተዳደር	150,000.00				150,000.00	238,377.22		238,377.22	388,377.22
2	የእቅድ ውጤታማነት						10,123.93		10,123.93	10,123.93
3	የካቢኔ ሴክሬታሪያትና የህግ ጉዳዮች						11,963.67		11,963.67	11,963.67

የፌደራል ዋና ኦዲተር

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ

1.1 ተልዕኮ

የሙያ ነፃነትን የቡድን ሥራንና ሀቀኝነትን መሠረት ያደረገ ሰፊ ሽፋንና ጥራት ያለው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ወቅታዊ የኦዲት አገልግሎት በመስጠት ተጠያቂነትን በማጠናከር፣መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና የመንግሥትን የአፈጻጸም ብቃት ለማሳደግ እገዛ ማድረግ፡፡

1.2 ራዕይ

በ2017 ዓ.ም በአፍሪካ ካሉት ምርጥ ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች አንዱ መሆን፡፡

2. ከ10ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በመሆኑ በአምስቱ አመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታን ለማጠናከር የኦዲት ሥርዓት፣ጥራት፣ ሽፋንና ክትትልን በማሣደግ በማጠናከር ተጠያቂነትን ማጠናከር፤ ኢንቨስትመንትን ከመሳብና ከማስፋፋት አንፃር የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚመራበትን የኦዲትና የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች በማዉጣት ለዕቅዱ መሳካት ወሳኝ የሆነዉን ሃብት በማሰባሰብም ሆነ በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን በማረጋገጥ ረገድ ም/ቤቱ የተጣለበትን ከፍተኛ ኃላፊነት እንዲወጣ ወቅታዊ አስተማማኝና ጥራት ያለዉ መረጃ በማቅረብ ለአምስቱ ዓመት ዕቅድ መሳካት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

መ/ቤቱ ሁለት ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን ለፕሮግራሞቹ ማስፈጸሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 115.91 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 100.00 ሚሊዮን በድምሩ ብር 215.91 ሚሊዮን ተደግፏል፡፡

4. ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች ውጤቶች ማጠቃለያ

ዓላማዎች	ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1 መ/ቤቱ በህግ የተሠጠውን ሀላፊነት በሚገባ ለመወጣት የሚያስችለውን አመራርና ድጋፍ መስጠት፡፡	**ፕሮግራም1፡ ስራ አመራርና አስተዳደር** በዚህ ፕሮግራም ሥር - የመ/ቤቱን ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች ማዘጋጀት፣ክትትልና ግምገማ ግብረ መልስ ማድረግ - የዉስጥ ኦዲት ማከናወንና ሪፖርት ማዘጋጀት - የህግ ምክርና አገልግሎት መስጠት - የፋይናንስ፣ግዢና ንብረት አስተዳደር - የሰው ሃብት ሥራ አመራር - የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት - የውጪና የህዝብ ግንኙነት ማጠናከር - ትምህርትና ስልጠና መስጠት - የወጪና የህዝብ ግንኙነት ማጠናከር - የለውጥ ስራዎችን መስራት ይከናወናሉ፡፡	➢ የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች	በመቶኛ	100

ዓላማዎች	ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 2 የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሽፋንን ወደ 100% ማሳደግ የክዋኔና የአካባቢ ኦዲት ሪፖርቶችን ቁጥር ከ36 ከፍ ማድረግ የሚከናወኑ ኦዲቶች በተቀመጠው ደረጃ (Standards) መሠረት እንዲሆን ማድረግ	**ፕሮግራም 2፡ የኦዲት ምርምርና ስርፀት** በዚህ ፕሮግራም ሥር • የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ • የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ • የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ • የአቅም ግንባታ መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ • የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ • ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ • ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡	➢ የተካሄደ የፋይናንሺያል ኦዲት ➢ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ➢ የተደረጉ የኦዲት ጥራት ሪፖ‘ርቶች ብዛት	በቁጥር በቁጥር በቁጥር	224 316 67

5. የ2015 ለመስሪያ ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራም ስም	ካፒታል					መደበኛ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግ/ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ከውጭ እርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግ/ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ድምር	
1	*2*	*3*	*4*	*5*	*6*	*7=3+4+5+6*	*8*	*9*	*10*	*11=7+10*
113	**የፊደራል ዋና ኦዲተር**	100,000.0				100,000.0	**115,905.75**			**215,905.75**
1	**ሥራ አመራርና አስተዳደር**	100,000.0				100,000.0	24,446.40			24,446.40
2	**የኦዲት ምርምርና ስርጸት**						91,459.35			91,459.35

የፌዴሬሽን ም/ቤት

1. የመ/ቤቱ ተልኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

ሕገ መንግሥቱን በመተርጎም፣ሕገ መንግስታዊ መብቶችን በማስከበር፣በክልሎች መካከል ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ግንኙነቶችን በማዳበር፣ፍትሃዊና ውጤታማ የድጎማና የጋራ ገቢዎች ማከፋፈያ ቀመሮች በማዘጋጀትና በመወሰን፣ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሓ ብሔር ጉዳዮችን በማጥናትና በመለየት፣ዜጎች ሕገ መንግሥቱን ጠንቅቀው አውቀው እንዲያከብሩና እንዲያስከብሩ በማድረግ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንድነት ሥር እንዲሠድና እንዲዳብር ማድረግ፡፡

1.2 ራዕይ

በሕገ መንግስቱ ለተረጋገጠው፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት ዘብ የቆመ ምክር ቤት ሆኖ ማየት፣

2. ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

ምክር ቤቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫ የሆኑትን የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማስከበር አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያግዙ ተግባራትን ለማከናወን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡ ከእነዚህም ተግባራት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የህገ መንግስት ግንዛቤ በህብረተሰቡ ውስጥ ማስረፅ፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ባህል መንከባከብ፣ በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ግንኙነት ላይ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ማስወገድና የጋራ ገቢዎችን ክልሎችን በማሣተፍ ተቀባይነት ያለው ፍትሀዊ የማከፋፈያ ቀመር ማዘጋጀት ናቸው፡፡

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

ም/ቤቱ በ5 ፕሮግራሞች የተዋቀረ ሲሆን ለእነዚህ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 96.65 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 150.00 ሚሊዮን በድምሩ ብር 246.65 ሚሊዮን ተደግፏል፡፡

4. የመ/ቤቱ ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች እና ግቦች

ዓላማዎች	ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1 ከ2013-2015 ምክር ቤቱ የተጣለበትን ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችል ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎትና በጥናትና ምርምር የተደገፈ ሙያዊ ምክረ ሀሳብ ማቅረብ	**ፕሮግራም 1፡- ሥራ አመራርና አስተዳደር** በዚህ ፕሮግራም ስር የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር፣ የፋይናንስ ግዥና ንብረት አገልግሎት፣ የኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎቶች፣ የኦዲት አገልግሎት፣ የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ የማድረግ፣ የስርዓተ ፆታን አፈፃፀም የማሻሻልና የህግ አገልግሎት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡	➢ የተሰጡ ድጋፍና አገልግሎቶች	በመቶኛ	100
ዓላማ 2 ከ2013-2015 የሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች አቤቱታዎች ላይ የሚደረግ ጥናትና ምርመራን ጥራት፣ መጠን፣ ጊዜንና ደረጃ በማሻሻል ተገልጋዮች ወቅታዊ እና የሚያረካ ምላሽ እና ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ	**ፕሮግራም 2፡- የሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች አገልግሎት** በዚህ ፕሮግራም ስር አቤቱታዎችን ተቀብሎ መመርመርና ጥናት ማድረግ፣ በይግባኝ አቤቱታዎች ላይ አስተያየት መስጠት፣በሕገ መንግስታዊ የማንነት ጥያቄዎች አጠናን፣ አፈታትና ምላሽ አሰጣጥ ላይ ወጥ የአሰራር ስርዓት እንዲለይ የማድረግ እና የፌዴራሉና የክልሎች የፍትህ አካላት እና ሌሎችም ባለድርሻዎች የሚሳተፉባቸው ኮንፈረንሶች/አውደጥናቶችን የማካሄድ ስራዎች ይካሄዳሉ፡፡	➢ ምላሽ ያገኙ የሕገ መንግስት ይግባኝ አቤቱታዎች ➢ ለመብት አቤቱታ ምላሽ የተሰጠ ሙያዊ አስተያየት፣ምክር ና ድጋፍ	በመቶኛ በመቶኛ	100 100
ዓላማ 3 ከ2013-2015 በመፈቃቀድና በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተ የብሔሮች ብሔረሰቦች እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነትን በላቀ ደረጃ ማጠናከር	**ፕሮግራም 3፡- የግጭት አፈታት፣ የሰላም እሴቶች ጥናትና ንቃተ ሕገ መንግስት** በዚህ ፕሮግራም ስር በክልሎች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመቀነስ የግጭት ካርታ ማዘጋጀት፣ አለመግባባቶች ወደ ግጭት እንዳያመሩ ቀድሞ የመከላከል ስራዎች መስራት እና የሚከሰቱ ግጭቶችንም ለመፍታት የባህላዊ ዘዴዎችን ከዘመናዊው ጋር በማጣመር ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡	➢ የተፈታ ግጭትና የተገነባ ሠላም ➢ የጎለበተ ንቃተ ሕገመንግስት	በመቶኛ በመቶኛ	50 50

ዓላማዎች	ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 4 ከ2013-2015 ፍትሃዊ፣ሁሉን አቀፍና አሳታፊ የሆነ የድጎማና የጋራ ገቢዎች ቀመር ማዘጋጀት	**ፕሮግራም 4፡- የድጎማ በጀትና የጋራ ገቢዎች ክፍፍል** በዚህ ፕሮግራም ስር የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች የሚሰጠውን ድጎማ እንዲሁም ለፌዴራል መንግሥትና ለክልል መንግሥታት የጋራ ተብለው የተለዩት ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈልበት ቀመሮች የማዘጋጀት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡	• የተከለሰ የጋራ ገቢዎች ማከፋፈያ ቀመር	በመቶኛ	40
		• የተካሄደ ጥናት	በቁጥር	1
		• የተከለሰ የፌዴራል ድጎማ ማከፋፈያ ቀመር	በመቶኛ	20
		• የተካሄደ ጥናት	በቁጥር	1
		• የተመጣጠነ የክልሎች እድገት ጋር ተያይዞ የተካሄደ ጥናት	በቁጥር	1
ዓላማ 5 ከ2013-2015 የገፅታ ግንባታና ወቅታዊ መረጃ ለህዝብ ተደራሽ የሆነ ተቋም	**ፕሮግራም 5፡- ግንኙነትና አጋርነት** በዚህ ፕሮግራም ስር ም/ቤቱ በህብረተሰቡ ዘንድ ይበልጥ የሚተዋወቅበት፣ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት ፓርላማዎች፣ተባባሪ እና አጋሮች ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች ለማጠናከር የሚያስችሉ፣ ም/ቤቱን የሚያስተዋውቁና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችን የሚያጎለብቱ ለሀገር መልካም ገጽታ ግንባታ ወሳኝ ድርሻ የሚያበረክቱ ተግባራትን የማከናወን ስራዎች ይከናወናሉ፡፡	• የተገነባና ተደራሽ የሆነ ተቋም	በመቶኛ	80
		• የተጠናከረ ፓርላሜንታዊ ዲፕሎማሲ	በመቶኛ	85
		• በአግባቡ የተከናወኑ ሁነቶች እና ኮንፈረንሶች	በመቶኛ	100

5. የ2015 ለመስሪያ ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

ፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	ካፒታል					መ ደ በ ኛ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግ/ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግ/ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11=7+10
114	የፊዴራሽን ምክር ቤት	150,000				150,000	96,651.67		96,651.67	246,651.67
1	ሥራ አመራርና አስተዳደር	150,000				150,000	51,365.17		51,365.17	51,365.17
2	የህገ መንግስት ትርጉምና መብቶች አገልግሎት						5,907.10		5,907.10	5,907.10
3	የግጭት አፈታት፣ የሰላም እሴቶች ጥናትና ንቃተ ሕገመንግስት						20,184.38		20,184.38	20,184.38
4	የድጎማ በጀት፣ የጋራ ገቢዎችና የሒሳብ ክፍፍል አዋጅ						6,855.02		6,855.02	6,855.02
6	ግንኙነትና አጋርነት						12,340.00		12,340.00	12,340.00

የቤተ መንግስት አስተዳደር

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

የቤተመንግስት አስተዳደር ቤተመንግስቶችን የማስተዳደር እና ቅርሶችን የመጠበቅ፣ የመንግስት መስተንግዶዎችን ማስተባበርና ማስፈጸም፣ የቤተመንግስት ቅርሶችን የቱሪስት መስህብ ክፍት በማድረግ ለአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ እንግዶች ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት ታሪክን ማስተዋወቅ፣ በሥሩ የሚገኙ ይዞታዎች ላይ የገቢ ማስገኛ ሥራ በማከናወን ወጭ የመደጎምና ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቱን እያጎለበተ በመጠቀም የድርሻውን መወጣት ነው።

1.2 ራዕይ

በ2020 ዓ.ም ምርጥ የአፍርካ ቤተመንግስት ሆኖ ማየት

2. ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

በልማት ዕቅድ ሰነድ ውስጥ መ/ቤቱን በሚመለከት በቀጥታ ተለይቶ የተቀመጠ የልማት ግብ ይኖርም፣ በአዋጅ ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት

- **መንግስታዊ መስተንግዶዎችን በላቀ ደረጃ በማከናወን ሀገራችን ያካበተችውን መልካም የውጭ ግንኙነት የማዳበር፣**
- **ሙዚየምን በማደራጀት ታሪክንና ትውፊትንና ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ የበኩሉን ድርሻ መወጣት፣**
- **ሙዚዬሞችን በማደራጀትና ለህዝብ ለጉብኝት ክፍት በማድረግ ታሪክንና ትውፊትን ለትውልድ ለማስተላለፍ የበኩሉን ድርሻ መወጣት**
- **ታሪካዊ ቅርሶችንና ሙዚየሞችን የመጠበቅ፣**
- **ሙዚየሞችን በማስፋፋት ለቱሪስት ክፍት እንዲሆኑ የማድረግና**
- **አስተዳደራዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ከማሳደግ አንፃር የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል።።**

3. የ2015 **በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ**

ለባለበጀት መ/ቤቱ 2015 በጀት ዓመት 3 ፕሮግራሞች ለመደበኛ ወጪ 393.08 ሚሊዮን ብር ከመንግስት ግ/ቤትና ከውስጥ ገቢ እንዲሁም ለካፒታል ፕሮጀክት 555.00 ሚሊዮን ብር ከመንግስት ግ/ቤት በድምሩ 948.08 ሚሊዮን ብር ተደግፏል። ።

4. የመ/ቤቱ ዓላማዎች፣ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች እና ግቦች

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች /የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1፡ ቤተመንግስቱ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲወጣ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመንግስት መስተንግዶዎችን ማስተባበር፣ ታሪካዊ ሕንፃዎችንና ቅርሶችን መከባከብ እና መጠበቅ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት	**ፕሮግራም 1፡ ሥራ አመራርና አስተዳደር** የአስተዳዳር፤ ስራ-አመራር ፤ ድጋፍና አገልግሎትን ማሻሻል ነው፡፡	• የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎት	በመቶኛ	100
ዓላማ 2፡ ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት ባሉት ዓመታት ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የመስተንግዶ አገልግሎት በመሥጠት የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ እንግዶችን ፍላጐት ማርካት	**ፕሮግራም 2፡ መስተንግዶ አገልግሎት** በጥራቱ ፈጣንና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ የተሰጠ የመስተንግዶ አገልግሎትና የተገኘ ገቢን ማሳደግ ነው፡፡	• የተሰጠ የመስተንግዶ አገልግሎት • የተገነቡና የተጠገኑ የእንግዳ ማረፊያ ቤቶች	በቁጥር በቁጥር	**113,135** 6
ዓላማ 3፡ ከ2013 እስከ 2015 ባሉት ዓመታት የቤተመንግሥቱን ቅርሶች፣ እንክብካቤና ጥበቃ በማድረግ ታሪካዊ ይዘታቸውን ይዞ ማቆየት	**ፕሮግራም 3፡ ሙዚየምና ቅርስ ክብካቤና ጥበቃ** በእንክብካቤ የተያዙ ቅርሶችን በጥራት፤ ፍጥነትና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ በማስተዳደር ከተሰጠ የፈረስ ኪራይና የመዝናኛ አገልግሎቶች የተገኘ ገቢን መሰብሰብ ነው፡፡	• የተከናወነ የቅርስ እንክብካቤና ጥበቃ ስራ • የተጠገኑ የቅርስ ህንፃዎች	በቁጥር በቁጥር	6 3

5. የ2015 ለመስሪያ ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	የ ካ ፒ ታ ል ወጪ					የ መ ደ በ ኛ ወ ጪ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግሥት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግሥት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10	11=7+10
116	**የቤተ-መንግስት አስተዳደር**	555,000.00				555,000.00	343,077.66	50,000.00	393,077.66	948,077.66
1	**የሥራ አመራርና አስተዳደር**						173,311.61		173,311.61	173,311.61
2	**የመስተንግዶ አገልግሎት**	449,895.50				449,895.50	133,858.50	46,700.00	180,558.50	630,454.00
3	**የሙዚየምና ቅርስ ክብካቤና ጥበቃ**	105,104.50				105,104.50	35,907.55	3,300.00	39,207.55	144,312.05

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮ እና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሕብረተሰቡን የሥነ-ዜጋ ግንዛቤ በማሳደግ፣ የመምረጥና የመመረጥ መብቱን በማስከበር፣ በሀገሪቱ ሁሉንም ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእኩልነት ያሳተፈ ፍትሃዊ፣ዴሞክራሲያዊ፣ነፃና ገለልተኛ ምርጫን በህጉ መሠረት በብቃት ማስፈፀም፡፡

1.2 ራዕይ

በ2017 ዓ.ም ምርጫን በማስፈፀም ብቃቱ በአፍሪካ ግንባር ቀደም ከሚባሉ ሃገሮች ተርታ ደርሶ ማየት፡፡

2. ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

ሀገራችን አሁን ለደረሰችበት የእድገት ደረጃ ልትደርስ የቻለችው ባለፉት ዓመታት በተከናወኑ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ውጤት መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የሀገራችን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዕውን ለማድረግና የልማት ሂደቱን በቀጣይነት ለማረጋገጥ ለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ የሚከናወኑትን ስራዎችና የሚያስገኙትን ውጤት መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ነፃ እና ፍትሀዊ ምርጫ ማከናወኑ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ዋነኛ ምሰሶ ሲሆን ዜጎች በመረጧቸው አስተዳዳሪዎች የመመራት መብታቸውን የሚያረጋግጡበት መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም ቦርዱ የዜጎችን መብት በተሟላ መልኩ ለማስከበር የምርጫ ስራዎችን በባለድርሻ አካላት በተለይ ደግሞ በመራጩ ሕዝብ ተአማኒነቱንና ተቀባይነቱን በቀጣይነት በማረጋገጥ ከዕቅዱ ጋር በማጣጣም በመስኩ የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

ጽ/ቤቱ ሁለት ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን ለፕሮግራሞቹ ማስፈጸሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 212.00 ሚሊዮን ተደግፏል፡፡

4. የዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞችና ውጤቶች ማጠቃለያ

ዓላማዎች	ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1 ከ2013-2015 በስታንዳርዱ መሠረት ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በ2012 ከነበረበት 95% ወደ 100% ከፍ ማድረግ	**ፕሮግራም 1፡- የሥራ አመራርና አስተዳደር** በዚህ ፕሮግራም ስር የሚከናወኑ ተግባራት እንዲፈፀሙ ልዩ ልዩ ድጋፍ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡	➢ የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች	➢ የአገልግሎት ሽፋን በመቶኛ ➢ አገልግሎት ያገኙ ደንበኞች ብዛት በመቶኛ	100 100
ዓላማ 2 የምርጫ አሠራር ስርዓትን በማመቻቸት መራጩን ሕዝብና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ በ2012 ከነበረበት 90% ወደ 95% በማሳደግ ምርጫውን ነፃ ፍትሀዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ እንዲሆን ማድረግ	**ፕሮግራም 2፡- ፍትሀዊ ምርጫ** በዚህ ፕሮግራም ስር በህዝብ የተመረጠ መንግስት እንዲቋቋም ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡	➢ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት	➢ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች ብዛት በቁጥር ➢ የተሰጠ የፓርቲዎች የፋይናንስ ድጋፍ በመቶኛ ➢ የተዘጋጁ የስልጠና ሠነዶች በቁጥር ➢ የመረጃ ተደራሽነት በመቶኛ ➢ የሴቶችና አካል ጉዳተኞ ተሳትፎ በመቶኛ	53,903,023 100 2 100 100

5. የ2015 ለመ/ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

የመ/ቤቱ /የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	የካፒታል ወጪ					የመደበኛ ወጪ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10=8+9	11=7+10
117	ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ						212,000.00		212,000.00	212,000.00
1	ሥራ አመራርና አስተዳደር						41,834.11		41,834.11	41,834.11
2	ፍትሀዊ ምርጫ						170,165.89		170,165.89	170,165.89

የሰላም ሚኒስቴር

1.የመስሪያ ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

የፌዴራልና የክልል መንግስታት አካላት ጋር በመተባበር መስራት፤የሀገርና ሕዝብ ሰላም ደህንነትና ነፃነት እንዲከበሩ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤የግንዛቤና የንቅናቄ ስራዎችን ማከናወን፤በተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች እንዲሁም በተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት ፤የባህልና ሃይማኖት ተቋማት ጋር በመተባበር መስራት ፤ለክልሎች በተለይም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት በመስጠት ድጋፍ ማድረግ ፤ሌሎች የፌዴራል መንግስት አካላት ለአርብቶአደር እና ለከፊል አርብቶአደር አካባቢ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የሚያደርጎቸውን ድጋፎች ማስተባበር ፤ማቀናጀት እና አፈጻጸሙን መከታተል ዋናዎቹ ናቸው፡፡

1.2 ራዕይ

ማህበራዊ ሃብታችንን በመጠቀም ህዝብንና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍና በማስተባበር የሰላም ባህል በመገንባት የህግ የበላይነትን በማስከበር ፍትህን በማስፈን እና ሀገራዊ መገንባት፡፡

2. ከ10 ዓመት የልማት እቅድ ጋር ያለዉ ግንኙነት

ተቋሙ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ከማሳካት አንፃር የሰላም ማዕከል መገንባት ፤አዳዲስ የሰላም አደራጃጀቶችን መፍጠር የፀረ አክራሪነት ስትራቴጂ መፍጠር ፤የግጭትና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ፈጣን ምላሽ መረጃዎችን በመተንተን ዘመናዊ የመረጃ ቅብብሎሽ እንዲተገበር የተደረገ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም በሰላም ባህል ግንባታና በአገራዊ መግባባት ላይ ቀመሮች ማካሄድ ናቸው፡፡

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

የሰላም ሚኒስቴር በ2015 በጀት ዓመት ለቀረባቸው 5 ፕሮግራሞች ማሰፈፀሚያ ለመደበኛ ወጪ 117.2 ሚሊዮን ብር ለካፒታል 750.0 ሚሊዮን ብር በድምሩ 867.2 ሚሊዮን ብር ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፏል፡፡

4. **የመስሪያ ቤቱ ዓላማቼ ፕሮግራሞች እና ንዑስ ፕሮግራሞቼ ዉጤቶች እና ግቦች**

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	**የፕሮግራሞች የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ**	**የ2015 በጀት ዓመት**		
		ዉጤቶች	**አመላካች**	**ግቦች**
ዓላማ 1፡ - የአመራርና ድጋፍ አገልግሎቶችንበተፈለገው ጊዜ ቦታና መጠን ማቅረብ	**ፕሮግራም 1፡ - ስራ አመራርናአስተዳደር** • **በዚህ ፕሮግራም ስር** • **ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈፃፀሙን መከታተል ፋይናንስ ስርዓት ማሻሻል** • **ተቋማዊ ለውጥ ግንባታን በቀጣይነት ማካሄድ** • **የሰው ሀብት ልማት ማካሄድና የንብረት አስተዳደር የሴቶችን እኩል ተ-ቃሚነት ማሳደግ**	• **የተሰጠ የድጋፍ አገልግሎት**	በመቶኛ	100
ዓለማ 2፡ - በፌዴራሊዝም ዙሪያ ከ2013-2015 የፌዴራል ስርአቱን ማጠናከርና ማሻሻል	**ፕሮግራም 5፡ -የ ፌዴራሊዚምና አርብቶ አደር ልማት** **በዘ!ህፕሮግራም ስር ቃ – በክልሎች መካከልያ አለመግባባት እና መካረርን ወደ መልካም ግንኙነት መቀየር** • **በፌዴራልና በክልል የባለሙያዎችን አቅም መገንባት** • **ስልጠና በመስጠት የስራ ባህል ማሻሻል**	• **ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚነትና የተጠናከረ የፌዴራል ስርአት**	• **ተቋማዊ አደረጃጀቶችና ፎረሞች በቁጥር** • **በአርብቶአደርና ልዩ ድጋፍ ክልሎች የወጣቶችና ሴቶችን የስራ ባህል ለመለወጥ የተሰጠ የአሰልጣኞች ስልጠና** • **የፌዴራል፣ የአጎራባች፣ የአርብቶአደርና ልዩ ድጋፍ ክልሎች እቅድ የተሳኩ ግቦች በ%** • **በልዩ ድጋፍ ክልሎች እና አርብቶ አደር አካባቢዎች በክፍተት የተለዩ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ተቋማት**	4 825 90 125,000

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ዉጤቶች	አመላካች	ግቦች
ዓለማ 3፡-የህብረተሰቡን በሰላምአብሮየመኖርእሴትማጎል በት	ፕሮግራም 3፡ -የ ሰ ላ ምእ ሴት በዘ!ህ ፕሮግራም ስርቃ– • አዳዲስ የሰላም ተቋም ማደራጀት • የፀረ አክራሪነት ስትራቴጂ ማዘጋጀት	• የተፈ ጠረ ዘላቂ ሰላም	• ስልጠና የተሰጣቸው የመንግስትና የሰላም አደረጃጀቶች • የተቋቋሙ እና የተጠናከሩ አዳዲስ የሰላም አደረጃጀቶች • የተቀረጹና የተሸሻሉ ዘርፉን ሚመለከቱ የአሰራር ስርዓቶች፣	40,000 62,500 5
ዓለማ4 የዜጎችንየስብሃዊመብትጥሰትመ ቀነስ	ፕሮግራም 4፡ -የ ህግየ በላይነ ት በዘ!ህ ፕሮግራም ስር ቃ – • በግጭት የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ ማቋቋም • በተጋጭ ወገኖች መካከል የእርቀ ሰላም ኮንፈረንስ ማካሄድ • የህግ የበላይነት ማስከበር • መረጃዎችን መተንተን	የቀነሰ የዜጎች የግጭት ስጋት	• በቴክኖሎጂ የተደገፈ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ስርዓት የተዘረጋባቸው ክልሎች ብዛት በቁጥር • በግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች የተወሰዱ የፈጣን ምላሽ እርምጃዎች ትንተና በቁጥር • ቀርበው የተፈቱ ቅሬታዎች መቶኛ	3ክ ል ሎች 2 9%
ዓለማ 5፡-የተቋሙን የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ተደራሽ ማድረግ	ፕሮግራም 5፡ -ዘ ማ ዊ የ ሚ ጃና ቁ ጥ ጥ ር ስ ር ዓ ት ማ ዘ ር ጋ ት በዘ!ህፕሮግራም ስርቃ የብሄራዊ የደህንነት ኮሙኒኬሽን ኔትወርክ መዘርጋት፣ ሀገራዊ የመሳሪያ ምዝገባ መረጃ ቋት ማዘጋጀት፣ ብሄራዊ መታወቂያ ስርሃት ለመዘርጋት የቅድመ ዝግጅት ስራ ማከናወን፣ የሰላም ማዕከል መገንባት	• የተዘረጋ ቀልጣፋ አገልግሎት	• ስልጠና የተሰጣቸው አመራርና ባለሙያዎች • ዘመናዊ የሰው ሃብት ሲስተም /ICMIS/ ተግባራዊ ማድረግ • የተዘረጋ የብሄራዊ መታወቂያ ስርአት • በተቀመሩና እውቅና ባገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች ተጠቀሚ የሆኑ አባ እና እማ ወራዎች	1030 10 10 10,000

5 . የ2015 ለመስሪያ ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሽ!ህ ብር

የመስሪያ ቤቱ መለያ ቁጥር	የፕሮግራም ስም	ካ ፒ ታ ል ወጪ					መ ደ በ ኛ ወጪ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከመስሪያቤቱ የዉስጥ ገቢ	ከዉጭ እርዳታ	ከዉጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከመስሪያቤቱ የዉስጥ ገቢ	ድምር	
118	የሰላም ሚኒስቴር	750,050.000	-	-	-	750,050.000	117,225.073	-	117,225.073	867,275.073
1	ስራ አመራርና አስተዳደር	--	-	-	-	-	55,700.000	-	55,700.000	55,700.000
2	ፌደራሊዝምና አርብቶአደር	-	-	-	-	-	9,025.293	-	9,025.293	9,025.293
3	የ ሰ ላ ምእ ሴት	750,050.000	-	-	-	750,050.000	17,736.000	-	17,736.000	767,786.000
4	የህግየበላይነት	-	-	-	-	-	16,050.780	-	16,050.780	16,050.780
5	አሰራርንማዘመን	-	-	-	-	-	18,713.000	-	18,713.000	18,713.000

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

ሕገ መንግስቱንና ሌሎች ህጎችን በማክበርና በማስከበር በህዝቦች ተሳትፎ ወንጀልንና የወንጀል ስጋቶችን በመከላከልና ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ ለህገራችን እድገትና ብልጽግና የድርሻውን ማበርከት፣

1.2 ራዕይ

በ2017 ዓ/ም የህዝባችንን እርካታና አመኔታ ያረጋገጠ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፖሊስ አገልግሎት ማየት፣

2. ከ10 ዓመቱ ሚሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

መንግስት ለሚቀጥሉት አምስት አመታት ያዘጋጀውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ውጤታማ ለማድረግ እንዲችል ከተቋሙ ተልዕኮ አንጻር በአገራችን ለኢኮኖሚ እድገትና ኢንቨስትመንት መስፋፋት የተረጋጋ ሰላምና ፀጥታ እንዲኖር ከተለያዩ የፌዴራልና የክልል ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተቋሙ ስትራቴጂክ እቅድና አመታዊ የፀጥታ እቅድ በማዘጋጀት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል።

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በ2015 በጀት ዓመት ለቀረፃቸው 5 ፕሮግራሞች እና 8 ንዑስ ፕሮግራሞች ማሰፈፀሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 6,100.33 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 734,145.72 ሚሊዮን በድምሩ ብር 6,835.1 ሚሊዮን ተደግፏል።

4. የዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶችና ግቦች

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1፡- የተቋሙን ዓላማና ተልዕኮ ለማስፈጸም ከፌዴራል፣ ከክልል፣ ከዞን እና አለም አቀፍ የጸጥታ ተቋማት ጋር የአጋርነትና የግንኙነት ሚና ማጠናከር እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶችን በጊዜ ሰሌዳ መሰረት መሰጠት	ፕሮግራም 1፡ ሥራ አመራርና አስተዳደር የተቋሙ አመራርና የድጋፍ አገልግሎት ፕሮግራም የፌዴራል ፖሊሲን ተልዕኮ ለማስፈጸም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን የመምራትና አስተዳደራዊና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚከናወንበት ነው፡፡	• የተሰጠ ድጋፍ • ካፒታል ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ	በመቶኛ በመቶኛ	100 100
ዓላማ 2፡- ከ 2013-2015 አሁን የሚኘውን የፎረንሲክ ምርመራ አሰራር ዘመናዊ በሆነ መልክ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመታገዝ ወንጀሎችንና ተዛማጅ ጉዳዮችን በብቃት መመርመር የሚያስችል አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ዓለም አቀፍ የፎረንሲክ ምርመራ አቅምን ማሳደግ	ፕሮግራም 2፡ ወንጀልና ፎረንሲክ ምርመራ በፌዴራል ደረጃ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ስለወንጀሉ አፈጻጸም በመሳሪያ በሚታገዝ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ምርመራ በማካሄድ ወንጀል ፈጻሚዎችን በትክክል በመለየት የፍትህ ስርዓቱ የፍርድ ሂደት ጠንካራ የሚያደርግ እንዲሁም ወንጀል ፈጻሚዎች ወደ ሕግ በማቅረብ አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ	• የተከናወኑ የወንጀል ምርመራ መዝገቦች • የተከናወኑ የፎረንሲክ ምርመራ	በቁጥር በቁጥር	3000 300,000
	ፕሮግራም 3፡ ወንጀል መከላከል			

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 3.1፡- ከ2013-2015 የሃገሪቱን ህገመንግስት ህገመንግስት ስርዓቱንና ሌሎች ህጎችን በማክበርና በማስከበር እንዲሁም ህብረተሰቡን በወንጀል መከላከል በማሳተፍ የህዝቡንና የመንግስትን ሰላምንና ደህንነት መጠበቅና ማረጋገጥ	ንዑስ ፕሮግራም 3.1፡ የኦፕሬሽን ስራዎችን ማስተዳደር የዚህ ፕሮግራም ስራዎች ደረጃውን የጠበቀ የወንጀል መረጃ አሰባሰብ፣ ትንተና፣ አያያዝ ስርጭት ስርዓት መዘርጋትና ማሳደግ፣ የኢኮኖሚ ነክ የወንጀል እንቅስቃሴ የሀሰተኛ ገንዘቦች እና ሰነዶች ወንጀል መከታተል፣ መከላከልና በቁጥጥር ስር ማዋል፣ የዘርፉን የሬዲዮ ግንኙነትን ማሳደግና ማስፋፋት፣ እንዲሁም የፈንጂ ጥቃቶችን በብቃት የመከላከል ስራዎች ይከናወናሉ	• የተከናወኑ የወንጀል መከላከል ኦፕሬሽን ስራዎች	በመቶኛ	100
ዓላማ 3.2፡-ከ2013-2015 የአገሪቱን ህልውና የሚፈታተኑ ጥቃቶችንና ለወንጀል መከሰት ዕድል የሚሰጡ መልካም አጋጣሚዎችን በመከላከልና በመቆጣጠር ፀጥታና ህግን ማስከበርና ወንጀሎችን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ	ንዑስ ፕሮግራም 3.2፡ የፀጥታና ሕግ ማስከበር ሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴና ኢኮኖያዊ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸውን ትላልቅ ተቋማትና መሰረተ ልማቶች ላይ አስፈላጊውን የሰው ኃይል በመመደብና የቅርብ ክትትል በማድረግ የተጠናከረ የተቋማት ጥበቃ ስራን ማከናወን፣ እንዲሁም ህገ ወጥ ሰልፎችንና አድማዎችን አስቀደሞ የመከላከልና በፍጥነት የመቆጣጣር ብቃትንና አቅምን በማሳደግ፣ ፀረ ሰላም ኃይሎችንና ወንጀሎችን ተከታትሎ በቁጥጥር ስር ማዋል ለሕግ እንዲቀርቡ	• የተከናወነ የፀትና ህግ ማክበር እና ጥበቃ የተደረገባቸው ተቋሞችና ኬላዎች	በመቶኛ	100

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
	የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፣			
ዓላማ 3.3፡-ከ2013-2015በህዝባችን ላይ የሚቃጡ የሽብር ጥቃቶች፣ ከፍተኛ ወንጀሎችንና ድንገተኛ አደጋዎች በብቃት መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችሉ አቅሞችን በመፍጠርና በማጠናከር አሁን ካለው የሽብር ጥቃቶችንና የተደራጁ ወንጀሎችን እንዲቀንሱ ማድረግ	ንዑስ ፕሮግራም 3.3፡ ፀረ ሽብር /የተደራጁ ወንጀሎች ቁጥጥር የሽብር ጥቃቆችንና የተደራጁ ወንጀለኞችን የመከላከልና የመቆጣጠር አቅምን ማሳደግና እነዚህ ወንጀሎች በብቃት መከላከል የሚችል ልዩ ኃይል ማጠናከር ፣ የቦሌ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት የውስጥና ዙርያ ጥበቃ በሰው ኃይል በማቴሪያል ማጠናከር፣ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣኞችና የውጭ አገር እንግዶች (VIP) የጥበቃ፣ የአጀባና የቁጥጥር/ፖትሮል/ ተግባር ማከናወን፣ የፕሮግራሙ ዋነኛ ተግባራት ናቸው፡፡	• መከላከል የተደረገላቸው የሽብር ጥቃቶችና የተደራጁ ወንጀሎች እንዲሁም የተጠናከረ ጥበቃ የተደረገላቸው VIP የአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርቶች ኤምባሲዎች ወይም የመንግስት ተቋሞች	በመቶኛ	100
ዓላማ 3.4፡- ከ2013-2015 በአገሪቱ ባሉ የተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጠሩ ህግወጥ ንግዶችን፣የፀረ ሰላም እንቅስቃሴዎችና ግጭቶች በመቆጣጠር አሁን ካለበት የግጭት እንቅስቃሴ በታች እንዲሆን ማድረግ፣	ንዑስ ፕሮግራም 3.4፡ ፈጥኖ ደራሽ መሰረተ ልማት ባልተዘጋባቸው የድንበር አካባቢዎች የሚከሰቱ የሽብርተኞችን እንቅስቃሴ፣ የኮንትራባንድ እንቅስቃሴና የጎሳና የሃይማኖት ግጭቶች፣ ህገወጥ የሰውና የጦር መሳሪያ ዝውውር መቆጣጠር፣ እንዲሁም የሀገሪቱ እድገት ተከትሎ የሚገነቡና የሚስፋፉ መሰረተ ልማቶች ከማንኛውም አደጋ የመከላከል ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡	• መከላከልና ቁጥጥር የተደረጋላቸው ህገ ወጥ ንግዶችና የጦር መሳሪያ ዝውውር ግጭቶች ድንበር ዘለል ግጭቶች ድንበር ዘለል ወንጀሎች እና የተጠበቁ መሰረተ ልማቶችና ተቋሞች	በመቶኛ	100

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
	ፕሮግራም 4: ትምህርትና ስልጠና			
ዓላማ 4.1፡-ከ2013-2015 በፈዴራልና በክልል ፖሊስ አሁን የሚታየውን የከፍተኛ አመራር ክፍተት ለመሙላት በተለያዩ የፖሊስ ሙያ ዘርፎች አዲስ የዲግሪ መርሀ ግብር በዲፕሎማና በአጫጭር ስልጠናዎች 2007-2009 በማስጀመር በሚቀጥሉት 3 ዓመታት 869 ተማሪዎችን መቀበልናሰልጣኞችን ማስመረቅ ከዚህም ውስጥ 30% ሴቶች እንዲሰለጥኑ ማድረግ፡፡	ንዑስ ፕሮግራም 4.1፡ ስታፍ ኮሌጅ በፖሊስ ማኔጅመንትና በወንጀል መከላከል በድግሪ መርሀ ግብር የሚሰጡትን ትምህርቶች አስፋፍቶና አጠናክሮ መስጠት፡፡	• በመደበኛ ትምህርት ቅበላ የተደረገላቸው ተማሪዎች • የተሰጠ የማታ መርሃ ግብርና የልዩ ልዩ አጫጭር ስልጠናዎች	በቁጥር በቁጥር	1218 1144
ዓላማ 4.2፡-ከ2013-2015 የፎረንሲክ ምርመራ ሥልጠናዎችን በማዘጋጀትና በወንጀል ምርመራ አዲስ የድግሪ መርሀ ግብር በ2007 በማስጀመር በሚቀጥሉት 3 ዓመታት ሰልጣኞችን ማስመረቅ በድግሪ 100 ተማሪዎችን እንዲሁም በዲፕሎማ 100 በአጫጭር ስልጠናዎች 735 ተማሪዎችን ማስመረቅና ከዚህ ውስጥ 30% ሴቶች እንዲሰለጥኑ ማድረግ	ንዑስ ፕሮግራም 4.2፡ ወንጀልና ፎረንሲክ ምርመራ የወንጀል ምርመራ ሥራ በታክቲክና በፎረንሲክ ምርመራ የተደገፈ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡	• በፎረንሲክ ትምህርት ቅበላ ማድረግ እና ስልጠናዎች መስጠት • የመደበኛ ትምህርት ቅበላና መከታተያ	በቁጥር በቁጥር	305 204

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 4.3፡- ከ2013-2015 ዓ.ምበፌዴራል ፖሊስ ስር የሚገኙትን ሆስፒታሎችና ጤና ተቋማትን በህክምና ሙያ በሰለጠነ የሰው ኃይል ማጠናከር	ንዑስ ፕሮግራም 4.3፡ ጤና ሳይንስ የጤና መኮንንነትና የጠቅላላ ህኪም የሙያ ሥልጠና ማዘጋጀት ይከናወናል።	• የተሰጡ የማማከርና የተጠናከረ የማህበረሰብ ፖሊሲ አገልግሎቶች • የተከናወኑ ጥናትና የተቀመሩ ምርጥ ተሞክሮዎች	በቁጥር በቁጥር	4 6
ዓላማ 4.4ከ2013-2015 ዓ,ም የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የመማርና የማስተማር ስራዎችና የፌዴራል ፖሊስ ስራዎችን በጥናትና ምርምር ስራዎች መደገፍና ማማከር	ንዑስ ፕሮግራም 4.4፡ የጥናትና ምርምር እና የተቋማት ለውጥ ስራዎች የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅን የመማርና የማስተማር ስራዎችና የፌደራል ፖሊስ ስራዎች በጥናትና ምርምር ስራዎች መደገፍና ማገዝ እንዲሁም የማማከር አገልግሎቶችና የተቋማት ለውጥ ስራዎች አጠንክሮ መቀጠል	• የተከናወኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችና የተቀመሩ ምርጥ ተሞክሮዎች እና የተሰጡ የማማከር አገልግሎቶች	በቁጥር	6
ዓላማ 5፡-ከ2013-2015 ዓ,ም የህክምና አገልግሎቱን የህክምና፣ መሣሪያና የባለሙያ እጥረትን በማስወገድ በተመላላሽም ሆነ በመኝታ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት 80 በመቶ ማድረስ	ፕሮግራም 5፡ የጤና አገልግሎት	• ልዩ ልዩ ግብዓት በማቅረብ የቅድመ መከላከል ስራዎች ማከናወን • ለህክምና አገልግሎት የተሰጠ ልዩ ልዩ ግብዓትና አጠቃላየ የድጋፍ አገልግሎት በመቶኛ ማሳደግ	በመቶኛ በመቶኛ	100 1 100

5.የ2015 ለመ/ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	ካ ፒ ታ ል					መ ደ በ ኛ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግሥት ግምጃ ቤት	ከድር ጅት ገቢ	ከውጭ ዕርዳ ታ	ከው ጭ ብድ ር	ድምር	ከመንግሥት ግምጃ ቤት	ከድር ጅት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10	11=7+10
127	**ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን**	734,145.72				734,145.72	4,016,962.2		**6,100,936.33**	**6,835,082.05**
1	ሥራ አመራርና አስተዳደር					734,145.72	1,829,329.68		1,829,329.68	2,563,445.40
2	ወንጀል ምርመራ						285,619.45		285,619.45	285,619.45
3	ወንጀል መከላከል						3,636,021.87		3,636,021.87	3,636,021.87
3.1	ኦፕሬሽን						1,205,587.86		1,205,587.86	1,205,587.86
3.2	ፀጥታና ህግ ማክበር						539,575.08		539,575.08	539,575.08
3.3	ፀረ ሽብርና ምርመራ						532,326.13		532,326.13	532,326.13
3.4	ፈጥኖ ደራሽ						1,358,532.8		1,358,532.8	1,358,532.8
4	ጤና አገልግሎት						349,965.33		349,965.33	349,965.33
4.1	ህክምና አገልግት መስጠት						346,965.33		346,965.33	346,965.33
4.2	ቅድመ በሽታ መከላከል						3,000.00		3,000.00	3,000.00

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

በፍርድ ቤት ውሳኔ ወደ ማረሚያ ቤት የሚመጡ እስረኞችና ታራሚዎችን በመቀበል የተጠናከረ የጥበቃ ደህንነትና አስተዳደር፣ የመሠረታዊ ፍላጎት አገልግሎት፣የተሀድሶ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት በማከናወን ታራሚዎች የወንጀልን አስከፊነት አውቀውና ተረድተው ከአስከፊነቱም ተምረው አምራችና ህግ አክባሪ ዜጋ እንዲሆኑ በማድረግ ተቋሙ በወንጀል መከላከልና የህዝብ ሰላምና ደህንነትን በማረጋገጥ የበኩሉን ድርሻ መወጣት፡፡

1.2 ራዕይ

በ2017 መልካም አስተዳደር የሰፈነበት የህግ የበላይነትና የህግ ታራሚዎች ሰብአዊ መብት የሚከበርበት የታረመና የታነጸ አምራችና ህግ አክባሪ ዜጋ የሚፈራበት ተቋም መሆን፡፡

2. ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ትስስር

መንግስት ባቀደው የምዕተ ዓመቱ ዕቅድ መሰረት መ/ቤታችን የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት፡-

- ማረሚያ ቤቶች ታራሚዎችን በአግባቡ አርሞ ለማውጣት ሐገራዊ የታራሚዎች አያያዝና ጥበቃ እስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ማንኛውንም ታራሚ የሥነ ዜጋ ፣የሥነ ምግባር ፣ የአካዳሚክና የሙያ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ በማድረግ አምራችና ህግ አክባሪ እንዲሆኑ ማስቻል፣
- ታራሚዎች የልማት ሥራዎችን በመስራት ገቢያቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ማድረግ፣
- የታራሚዎች ሰብዓዊ መብት በአግባቡ እንዲጠበቅ ማድረግ፣
- የታራሚውን የመጠለያ ፣የምግብ፣የጤና እንክብካቤ፣ የግንኙነትና የመዝናኛ አገልግሎቶች እንዲሻሻሉ ማድረግ፣
- የማረሚያ ቤት ቆይታቸውን ጨርሰው የሚወጡ ታራሚዎች ከህብረተሰቡ ጋር ተዋህደው የሚሰሩበትን ሁኔታ የሚከታተል ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ናቸው፡፡

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በ2015 በጀት ዓመት በአራት ፕሮግራሞች የተዋቀረ ሲሆን ለዕቅዶቹም ማስፈጸሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 1,120.8 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 614.6 ሚሊዮን በድምሩ ብር 1,735.4 ሚሊዮን ተደግፎል፡፡

4. የመ/ቤቱ ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች እና ግቦች

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ1፡-ከ2013-2015 ዓ.ምግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር በማስፈን ተቋማዊ አቅምን ከ90% ወደ 95% በማሳደግና ውጤት ያለው የሰው ኃይል ለማብቃት ለሚደረገው የዕቅድ አፈጻፀም ተግባራዊነት ድጋፍ ማድረግ፡፡	ፕሮግራም 1፡ ሥራ አመራርና አስተዳደር፣ • በዚህ ፕሮግራም አንድ ውጤትና ዘጠኝ ዋና ዋና ተግባራት ያሉት ሲሆን በዚህም መሰረት መ/ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ለሚደረገው የሥራ እንቅስቃሴ እስትራቴጂካዊ አመራሮችን በመስጠት ለሥራው መቃናት ተገቢው የድጋፍ አገልግሎት የሚከናወንበት የሥራ ክፍል ነው፡	• የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች	በ ጦቶኛ	100
ዓላማ 2፡- ከ2013-2015ዓ.ም የ45,000 የህግ ታራሚዎችን የጥበቃ ደህንነትና የፍትህ አስተዳደር ሥራዎችን በመስራት ሰብአዊ መብታቸው በአግባቡ መጠበቁን ማረጋገጥ፡፡	ፕሮግራም 2፡ ጥበቃና ደህንነት • በዚህ ፕሮግራም አንድ ውጤትና አንድ ዋና ተግባራት ያሉት ሲሆን በዚህም መሰረት ሁሉም ቅርንጫፍ ማረሚያ ቤቶች በሚይዙት የታራሚ አይነት ለይቶ ማደራጀትና የጥበቃ ደህንነት ስምሪቱን ጥራቱን ጠብቆ ማከናወን እንዲሁም ታራሚውን በየጊዜው በቀጠሮአቸው ቀን ወደ ፍ/ቤቶች፣ ሆስፒታሎችና ሌሎች በፍ/ቤት ትዕዛዝ ለሚሰጡ ማህበራዊ አገልግሎቶች በማመመላለስ ለታራሚው ተገቢ የሆነ አገልግሎት የሚሰጥበት የሥራ ክፍል ነው፡፡	• በሁሉም ቅርንጫፍ ማረሚያ ቤቶች የተከናወነ የጥበቃ ደህንነትና የፍትህ አስተዳደር አገልግሎት	በቁጥር	15,000

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 3፡- ከ2013-2015 ዓ.ም ለ71,000 የህግ ታራሚዎች የተለያዩ ምህርትና ስልጠናዎችን በመስጠት የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ በማድረግ አምራችና ህግ አክባሪ ዜጋ እንዲሆኑ ማስቻል ።	**ፕሮግራም 3፡ ተሀድሶና ልማት** • በዚህ ፕሮግራም አንድ ውጤትና አንድ ዋና ዋና ተግባራት ያሉት ሲሆን በዚህም መሠረት የህግ ታራሚዎች በእርምት ቆይታቸው ወቅት በተለያዩ የቀለም ትምህርቶች፣ በሙያና ቴክኒክ፣ በምክር አገልግሎት፣ በንቃተ ህግና ሥነ-ምግባር፣ በስፖርትና መዝናኛ፣ እንዲሁም በግብርና ሙያዎች ስልጠናዎችን በመስጠት ዳግም ወደ ወንጀል ተግባር እንዳይሰማሩና ከህብረተሰቡም ጋር ሲቀላቀሉ ጤናማ አስተሳሰብ ይዘው አምራችና ህግ አክባሪ ዜጋ ሆነው እንዲወጡ ለማድረግ ከፍተኛ ሥራ የሚከናወንበት የሥራ ክፍል ነው።	▪ በሁሉም ማዕከል ማረ/ቤቶች የተከናወነ ማረምና ማነጽ	በቁጥር	13,000
ዓላማ 4፡- ከ2013-2015 ዓ.ም ለ48,000 የህግ ታራሚዎች ህግ የተፈቀደላቸውን መሠረታዊ ፍላጎቶችን በማሟላት ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ አሁን ካለበት 85%ወደ 100%ማድረስ።	**ፕሮግራም 4፡ መሠረታዊ ፍላጎት** ➢ በዚህ ፕሮግራም አንድ የመደበኛና አንድ የፕሮጀክት በድምሩ ሁለት ውጤቶችና እንዲሁም አንድ መደበኛ ተግባራትና አራት የፕሮጀክት ተግባራት በድምሩ አምስት ዋና ዋና ተግባራቶች ያሉት ሲሆን በዚህም መሠረት የህግ ታራሚዎች በእርምት ቆይታቸው ወቅት የህግ አግባቡ የሚፈቅድላቸውን የምግብ፣ የአልባሳት፣ የመጠለያ ቤትና የህክምና አገልግሎት በተሟላ መልኩ እንዲያገኙ ከፍተኛ ሥራዎች የሚከናወንበት የሥራ ክፍል ነው።	▪ በሁሉም ቅርንጫፍ ማረ/ቤቶች የተከናወነየመሠረታዊ ፍላጎት አቅርቦት ▪ የተከናወነ የታራሚዎች መኖሪያ ቤት ህንፃ ግንባታ	በቁጥር በፐርሰንት	15,000 15.7

5. የ2015 ለመ/ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

የመ/ቤቱ/የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	የካፒታል ወጪ					የመደበኛ ወጪ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10=8+9	11=7+10
129	**የፊዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር**	**614,580**				**614,580**	**1,120,809.5**		**1,120,809.5**	**1,735,389.48**
1	ሥራ አመራርና አስተዳደር፣						249,143.60		249,143.60	249,143.60
2	ጥበቃና ደህንነት						340,970.00		340,970.00	340,970.00
3	ተሀድሶና ልማት						245,058.24		245,058.24	245,058.24
4	መሠረታዊ ፍላጎት	614,580				614,580	285,637.7		285,637.7	285,637.7

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1. ተልዕኮ

የሰብዓዊ መብቶችን ማስተማርና ለሁሉም ሰዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ ::

1.2. ራዕይ

የሰብዓዊ መብቶች ባህል የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት::

2. ከ10 ዓመቱ ሚሪ የ ልማት እቅድ ጋር ያለው ትስስር

ኮሚሽኑ በአገር አቀፍ የልማት ዕቅድ ውስጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ በሰብአዊ መብቶች ማስከበርና ማክበር ረገድ ህዝባዊ ንቅናቄን መፍጠር፣ ሕዝባዊ ግንዛቤን በማስረጽ ንቃተ-ህሊናን የማጎልበት፣ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በመመርመር የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመስራት፣ በሰብአዊ መብት ወቅታዊ አያያዝ ዙሪያ ክትትል እና ጥናትና ምርምር በማከናወን መንግስትን የማማከር እንዲሁም ለሴቶችና ሌሎች ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የማሕበረሰብ ክፍሎች የተጋላጭነት ደረጃቸውን ለመቀነስ ጥረት በማድረግ ይቀጥላል፡፡ በተጨማሪም በአዲሶቹ ፕሮግራሞቹ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች፤ የማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መብቶች፤ በአካል ጉዳተኞችና በአረጋዊያን መብቶች፤ በአገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ተፈናቃዮችና ስደተኞች መብቶች ዙሪያ እንዲሁም በድንገተኛና በአደጋ ምክንያት ለሚከሰቱ የመብት ጥሰቶች የሚያከናውናቸው ስራዎች የሰብአዊ ልማትን የሚያግዙ ናቸው፡፡

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

ለ2015 በጀት ዓመት ለ4 ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 110.0 ሚሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፏል፡፡

4.መ/ቤቱ ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች እና ግቦች

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	*ፕሮግረሞች*	*የ2015 በጀት ዓመት*		
		ውጤቶች	*አመልካቾች*	*ግቦች*
ዓላማ 1፡- ተቋማዊ ሪፎርም፣ አቅም ግንባታና ዘላቂነት ናየኮሚሽኑን ዓላማ ለማሳካት ድጋፋዊ አገልግሎትን ማሳለጥ፡፡	***ፕሮግራም 1፡- የስራ አመራርና አስተዳደር***	**የተሰጠ ድጋፍና አገልግሎት**	**በቁጥር**	105
›§¥ 2፡- የባለ መብቶችንና የባለግዴታዎችን የሰብአዊ መብቶች እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ማጎልበት	***ፕሮግራም2፡- የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት***	➢ **የባለመብቶች እና የሲቪል ማህበራት መብታቸውን ለማስከበር የሚያስችላቸው የጎለበተ ዕውቀትና አቅም፤**	**በቁጥር**	1705
		➢ **የጎለበተ የባለግዴታዎች የሰ/መ የማክበር የመጠበቅና የማሟላት አቅምና ቁርጠኝነት፤**	**በቁጥር**	135
		➢ **ያደገ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት መደበኛ በሆኑና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች/ መርሃ ግብሮች/ ሥረዓት ተምህርቶች መካተት**		
		➢ **የሰ/መ/ትን ለማካተትና** ➢ **ለማስፋፋት ያደገ የቁልፍ ባለድርሻ አካላት መተጋገዝና ትብብር፤**		

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	ፕሮግረሞች	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
		➢ ያደገ የሠራተኞች የስ/መ/ት ፕሮግራሞችን የመቅረጽ የመተግበር፣ አፈጻጸምን የመከታተልና የመገምገም አቅም		
ዓላማ 03 የሴቶችና ህጻናት መብቶች ይስፋፋሉ፤ ይከበራሉ እንዲሁም ጥሰቶች ተገቢውን ምላሽ ያገኛሉ፤	ፕሮግራም 3፡- የድርጊት መርሃግብር - የሴቶችና ህጻናት ሰብዓዊ መብቶች	• የህግ ማዕቀፎችና አተገባበራቸው ከህገ መንግስቱ ከአህጉራዊና ከዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ደረጃዎች ጋር የሚስማሙ ሆነዋል፤	በቁጥር	4
		• የሴቶችና ህጻናት ሰብአዊ መብቶችን ለመከላከልና ለመጠበቅ የሚያስችል ያደገ የመብት አስከባሪዎች ግንዛቤና እንቅስቃሴ፤	በቁጥር	11
		• ባለመብቶች መብታቸውን ለመጠየቅ የሚያስችላቸው ያደገ አቅም፤		300
		• የባለ ግዴታዎች ለሴቶች እና ለህጻናት መብቶች ያለ የተሻሻለ ግዴታን መወጣት እና የተሻሻለ የሴቶች መብቶች አፈጻጸም፤		4
		• ያደገ ክቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ ትብብር እና የተቀናጀ ጥረት፤		

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	ፕሮግረሞች	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
		• በሴቶች መብቶች አከባበር ያደገ ተቋማዊ አቅም፤		
ዓላማ 4፡- የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች ይስፋፋሉ፤ ይከበራሉ እንዲሁም ጥሰቶች ተገቢውን ምላሽ ያገኛሉ፤	ፕሮግራም 4፡- የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያ መብቶች	የህግ ማዕቀፎችና አተገባበራቸው ከህገ መንግስቱ ከአህጉራዊና ከዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ደረጃዎች ጋር የሚስማሙ ሆነዋል፤	በቁጥር	38
		የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶችን ለመጠበቅና ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ያደገ የባለግዴታዎች ግንዛቤና እንቅስቃሴ፤	በቁጥር	8
		ባለመብቶች መብታቸውን ለመጠየቅ/ለማስከበር የሚያስችል ያደገ ብቃት፤	በቁጥር	19
		የተሻሻለ የባለግዴታዎች የሰብአዊ መብቶች ግዴታን መወጣት እና የተሻሻለ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች		15
		ያደገ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ ትብብር እና የተቀናጀ ጥረት፤		

5. የ2015 ለመ/ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

የመ/ቤቱ/ የፕሮግራ ም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	የካፒታል ወጪ					የመደበኛ ወጪ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከድርጅ ት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+ 5+6	8	9	10=8+9	11=7+10
132	**የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን**						**110,000**		**110,000**	**110,000**
1	የስራ አመራርና አስተዳደር						77,469.798		72,643.798	72,643.798
2	የሰብአዊ መብቶች ትምህረት እና ስልጠና						4,309.339		4,309.339	4,309.339
3	የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ ጉዳዮች						15,900.896		15,900.896	15,900.896
4	የሰብዓዊ መብቶች ዘርፉ						12,319.967		12,319.967	12,319.967

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1. ተልዕኮ

በአስፈፃሚ አካላት የሚወጡ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አሰራሮች ህገ-መንግስቱን የማይቃረኑ መሆናቸውን በመቆጣጠር፤ የአስተዳደራዊ በደል አቤቱታዎችን በመመርመር የመፍትሄ ሀሳብ በመሻት፤በነባር ሕጎችና አሰራሮች እንዲሻሻሉ፣ አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ በማሳሰብ፤ አስተዳደራዊ በደልን ለመከላከል የቁጥጥርና ጥናት ስራዎችን በማካሄድ ምክረ-ሃሳብ በማቅረብ፤ በመልካም የመንግስት አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ለመንግስት የምክር አገልግሎት በመስጠት፣ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ እና የመረጃ ነፃነት ህጉን ተግባራዊነት በመከታተል መልካም የመንግስት አስተዳደርን ማስፈን፡፡

1.2. ራዕይ

በ2017 ዓ.ም ፍትሃዊና ተጠያቂነት ያለዉ መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን በማድረግ ተዓማኒ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሆኖ መገኘት፡፡

2. ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በቀጣይ አምስት ዓመት ከሚያከናዉናቸዉ ዋና ዋና ተግባራት የአስተዳደራዊ በደል አቤቱታዎችን ተቀብሎ በመመርመር የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ፤አስተዳደራዊ በደልን ለመከላከል የቁጥጥርና ጥናት ስራዎችን ማከናወን፤የመረጃ ነፃነት ህጉን ተግባራዊነት መከታተልን፤ የሚወጡ መመሪያዎች፣ዉሳኔዎችና አሳራሮች ህገ-መንግስቱን የማይቃረኑ መሆኑን መከታተል፤ለህዝብ ጥቅም ሲባል ነባር ሕጎችና አሰራሮች እንዲሻሻሉ፤ አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ማሳሰብንና ልዩ ትኩረት የሚሹ ዜጎች የተሳታፊነትና ተጠቃሚነት መብት እንዲረጋገጥ ማድረግ ለዲሞክራሲና ለልማት የሚያገለግሉ ህጎች መውጣትና አፈጻጸማቸውን መከታተል መቆጣጠር ለተለያዩ ተቋማት የተሰጡ ሃላፊነቶች ናቸው፡፡

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

ለ2015 በጀት ዓመት ለ5 ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ ለመደበኛ ወጪ ብር 93.99 ሚሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፏል::

4. መ/ቤቱ ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች እና ግቦች

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1፡- ወቅታዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎትና ድጋፍ በመስጠት የተቋሙን አላማ እንዲሳካ ማድረግ፤	**ፕሮግራም 1፡- የሥራ አመራርና አስተዳደር** ይህ ፕሮግራም የተቋሙን ዋና ዋና ተግባራት የመምራትና አስተዳደራዊና ሌሎች አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ ሁኔታ የመከናወን ተግባራት የሚያከናውን ነው፡፡	▪ የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች	በመቶኛ	100
ዓላማ 2 ፡- በዕቅድ ዘመኑ በህጻናት ሴቶችና አካላ ጉዳተኞች የሚደርሱ አስተዳራደራዊ በደሎች እንዲቀንሱ ማድረግ	**ፕሮግራም 2፡- ልዩ ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች**	▪ የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር	በቁጥር	215
		▪ የተፈጠረ ግንዛቤ	በቁጥር	4950
ዓላማ 3፡- በዕቅድ ዘመኑ በህብረተሰቡ የሚደርሱ የአስተዳደራዊ በደሎች መቀነስ ነው	**ፕሮግራም 3፡- የአስተዳደር በደል መከላከል**	▪ የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር	በቁጥር	190
		▪ የተፈጠረ ግንዛቤ	በቁጥር	7230
ዓላማ 4፡- ማንኛውም መንግስታዊ አካል ዜጎች መረጃን ለመጠየቅ፣ለማግኘትና ለማስተላለፍ ያላቸው መብት እንዲጠቀሙ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ማጠናከር ነው	**ፕሮግራም 4፡- የመረጃ ነፃነት ማስተግበር ፕሮግራም**	▪ የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር	በቁጥር	679
		የተፈጠረ ግንዛቤ	በቁጥር	14000
ዓላማ 5 በዕቅድ ዘመኑ ከቀረቡት አቤቱታዎች በመቀበልና በመመርመር የተፈጸሙ አስተዳደራዊ በደሎች እንዲታረሙ ማድረግና የውሳኔ አሰጣጥ ወደ 100% ማሳደግ ነው፡፡	**ፕሮግራም 5፡- ምርመራና ማረም**	የተሰጡ መፍትሔዎችና የተደረጉ ምርመራዎች	በመቶኛ	84

5. የ2015 ለመ/ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

የመ/ቤቱ/ የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	የካፒታል ወጪ					የመደበኛ ወጪ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከድርጅት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10=8+9	11=7+10
133	የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም						93,991.800			93,991.800
1	የሥራ አመራርና አስተዳደር						58,862.802			58,862.802
2	ልዩ ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች						5,196.908			5,196.908
3	የአስተዳደር በደል መከላከል ፕሮግራም						9,657.785			8,657.785
4	የመረጃ ነፃነት ማስተግበር ፕሮግራም						11,837.822			11,837.822
5	ምርመራና ማረም						8,257.483			8,257.483

የፍትህ ሚኒስቴር

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

የህግ የበላይነትንና ሰብዓዊ መብትን በማክበርና በማስከበር፤ ወንጀልን በመከላከል፣ ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥና የመንግስትንና የህዝብን ጥቅም በማስጠበቅ፤ የሕዝብ ዓመኔታ ያተረፈ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ የፍትህ አገልግሎት መስጠት፡፡

1.2 ራዕይ

በ2022 የአፍሪካ የፍትሕ ተቋማት ተምሳሌት ሆኖ ማየት

2. ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

የፍትህ ሚ/ር በአዋጅ ቁጥር 943/2008 ቀደም ሲል በተለያዩ ተቋማት (ከቀድሞው የፍትህ ሚ/ር፣ ከገቢዎች ጉምሩክ፣ ከሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና እንዲሁም ከንግድ ሽማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን) ተበታትነው ይሠሩ የነበሩ የዓቃቤ ህግ ሥራዎችን በማጠቃለል አንድ ጠንካራ የህዝብና የመንግስት ጥቅም በተሟላ መልኩ የሚያስጠብቅ ህግ አስከባሪ ተቋም ሆኖ የተቋቋመ ሲሆን ተቋሙ በዋናነት ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በማክበር የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ዋና ዓላማው ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም ፡- ህገ መንግስቱን ማክበርና ማስከበር፣ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥና የወንጀል ህግን ማስከበር ናቸው

የፌዴራል መንግስትና የህዝብን የፍትሐብሔር ጥቅም ማስከበር ዝርዝር ዓላማዎች የያዘ ሲሆን ከሀገራዊ ሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አንጻር የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ የፍትህ አስተዳደር ሥርዓቱ ውጤታማነትና ከሙስና አድልዎ የፀዳ ከማድረግ አንጻር በፍትህ ሥርዓቱ የተረጋገጡና እውነተኛ ማስረጃዎችን በማቅረብ የፍትህን ውጤታማነት ማጠናከር፣ ህጎች ሲረቀቁና ሲሻሻሉ እንዲሁም አፈፃፀማቸውን አተረጓጎማቸውን ከህገ መንግስቱ ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

3. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

የፍትህ ሚኒስቴር 3 ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን ለመደበኛ ወጪ ብር 615.3 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 285.0 ሚሊዮን በድምሩ ብር 900.3 ሚሊዮን ተደግፏል፡ ፡

4. የዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞችና ውጤቶች እና ግቦች ማጠቃለያ

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካች	ግብ
ዓላማ 1 ከ(2013-2015) በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት በማድረግ አሁን ያለውን (71.4.%) የተገልጋይ ርካታ ወደ (90%) ማሳደግ፣ በተቋሙ የክትትልና ደጋፊ አመራር ሠጪነት አቅም በማጎልበት የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈፃፀምን በ 1.5% ማሳደግ፣ የማስፈፀም አቅምን በማሳደግ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለ 2700 ሰራተኞች መስጠት፣ የቅሬታ መስተንግዶ እና ምላሽ ሰጭነትን አሁን ካለበት ከ85% ወደ 95% ማሳደግ፣ የሴቶች ሕፃናትና የባለብዙ ለዘርፍ ተግባራት አፈፃፀምን አሁን ከሚገኝበት 80% ወደ 90% ማሳደግ።	ፕሮግራም 1፡ - ሥራ አመራርና አስተዳደር	➢ የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች	➢ ያደገ የተገልጋይ እርካታ በመቶኛ	82

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካች	ግብ
ዓላማ 2 ክ(2014-2015) ድረስ የወንጀል መከላከል ተግባራትን በማከናወን ወንጀልና ወንጀል ስጋትን በ0.7% መቀነስ፣ የወንጀል ምርመራ ተግባራትን ውጤታማ በማድረግ ክርክር የመርታት ምጣኔን አሁን ካለበት (91.1%) ወደ (94%)፣ በሴቶች ህጻናትና ወጣቶች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የመርታት ምጣኔን አሁን ካለበት (90%) ወደ (94%)፣ የመርታት/ሀብት የማስመለስ ምጣኔ አሁን ካለበት (90%) ወደ (95%)፣ የቀላል ወንጀል ጉዳዮች በዕርቅ እንዲቋጩ ማድረግ አሁን ከተደረሰበት (81.2%) ወደ (87%) ማድረስ፣ የወንጀል ፍሬና በሕግ የሚወረሱ ሀብትን የማስመለስ ውጤታማነትን በማሻሻል አፈፃፀሙን (95%) ማድረስ፣ የፍትሀብሄር ጉዳዮች ውጤታማነት እና የመርታት አፈፃፀም ከነበረበት (94.73%) ወደ (96%) ማሳደግ፣ ጠቋሚዎች፣ ምስክሮችና የወንጀል ተጎጂዎች ተሳትፎ፣ አያያዝና ጥበቃ አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል አፈፃፀሙን አሁን ከተደረሰበት (82%) ወደ (87%) ማሳደግ። ዓላማ3	ፕሮግራም 2፡ - ክርክር	➢ ያደገ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ➢ የፍትሐብሔር መብቱ የተከበረ ህዝብና መንግስት ➢ የተስተናገዱ የይቅርታ ጥያቄዎች ➢ ያደገ የህገ ወጥ ሰዎች ዝውውር ትምህርትና ግንዛቤ	➢ የማስቀጣት ምጣኔ ➢ የመርታት ምጣኔ ➢ በህግ መሠረት የተሠጠ ይቅርታ ➢ ተደራሽ የሆነ ትምህርትና ግንዛቤ	94.5 91.0 100 100

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካች	ግብ
ከ(2013-2015) በሕግ ምክር፣ በውል ምርመራ ድርድርና ክርክር የመንግስትና የህዝብ ፍትሀብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ አፈፃፀም አሁን ካለበት (80%) ወደ (90%) መድረስ፣ በህግ እና ፍትህ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብርን ማሳደግ የመንግስትና የሕዝብ ጥቅም (100%) ማስጠበቅ፣ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥና ዕድሳት አፈጻፀም (100%) ማድረስ፤ በጀት ዓመት የህግ ጥናት፣ ማርቀቅና ማስረፅ አፈጻጸም አሁን ካለበት (90%) ወደ (100%)፤ ለ80 ሺ ዜጎች የንቃተ ሕግ ትምህርት መስጠት፣ የፌዴራል ህጎች ተፈፃሚነት ክትትል አፈፃፀም (91%) ማድረስ፤ ነፃ የሕግ ምክርና አገልግሎት ለ3000 አቅመ ደካማ ዜጎች መስጠት፣ የይቅርታ አመክሮ አፈፃፀም ክትትል ውጤታማነት ማሻሻል፣ የይቅርታ አሠጣጥ ውጤታማነት አሁን ከሚገኝበት (94%) (98%) ማሳደግ፣ የሰብዓዊ መብት ማክበርና ማስከበር አፈፃፀም (100%) ማድረስ፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርና ፍልሰት መከላከልና መቆጣጠር አፈፃፀምን ማሳደግ፣ የብሔራዊ የተቀናጀ የፍትህ ሥርዓት ፕሮጀክት አፈፃፀም (50%) ማድረስ፡፡	ፕሮግራም 4፡ - የሕግ ጉዳዮች	➢ ያደገ የህግ ጥናት ማርቀቅ፣ ማስረፅ አተገባበር ➢ የተሰጠ የጥብቅና ፍቃድ እድሳትና ነፃ የህግ አገልግሎት ➢ የተተገበረ የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሀ ግብር ➢ የተሻሻለ የህግ አዲትና ኢንስፔክሽን አተገባበር	➢ በጥናት የተሻሻሉና የተረቀቁ ህጎች ➢ በመሥፈርቱ መሠረት የተሰጡ ፍቃድና እድሳት ➢ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ክትትል መርሀ ግብር ትግበራ ብዛት ➢ በህግ አዲት ውሳኔ የተሰጠባቸው መዛግብት	100% 100% 100% 100%

5. የ2015 ለመ/ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	ካ ፒ ታ ል					መ ደ በ ኛ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግሥት ግምጃ ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግሥት ግምጃ ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10	11=7+10
121	**የፍትህ ሚኒስቴር**	285,000.0	-	-	-	285,000.0	615,276.0	-	615,276.0	900,276.0
1	**ሥራ አመራርና አስተዳደር**	285,000.0	-	-	-	285,000.0	128,099.5	-	128,099.5	413,099.5
2	**ክርክር**	-	-	-	-	-	447,100.6	-	447,100.6	447,100.6
4	**የሕግ ጉዳዮች**	-	-		-	-	40,075.9	-	40,075.9	40,075.9

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች

1. **የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ**

1.1 **ተልዕኮ**

የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ህግን መሰረት ያደረገ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት፣

1.2 **ራዕይ**

በ2017 ሙሉ ለሙሉ የህዝብ ዓመኔታ የተቸረው ፍ/ቤት ሆኖ መገኘት ነው።

2. ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

በዕድገትና ትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ ሰነድ እንደተመለከተው ከፍትህ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል የዳኝነት ሥርዓትንና የፍርድ ቤቶችን ነፃነትን፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ አንደኛው ነው። የፍትህ ዘርፉ ዓላማዎች ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማስረፅና የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ ፍትህ መስጠት፣ የፍትህ ሥርዓቱን ነፃነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማረጋገጥ እንዲሁም ጠንካራና የተረጋጋ የፌዴራል ሥርዓት መገንባትና የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ ሲሆኑ እነዚህን ዓላማዎች ከማረጋገጥ አኳያ የዳኝነት አካሉ ከፍተኛ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል ።

2. የ2015 በጀት ድጋፍ ማጠቃለያ

የፌዴራል ፍ/ቤቶች በ 5 ፍ/ቤቶች የተዋቀረ ሲሆን ለእነዚህ ማስፈጸሚያ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለመደበኛ ወጪ ብር 171.2 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 275.7 ሚሊዮን በጠቅላላው ብር 446.9 ሚሊዮን ፣ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለመደበኛ ወጪ ብር 242.4 ሚሊዮን ፣ ለካፒታል ወጪ ብር 885.0 ሚሊዮን በጠቅላላው ብር 1.1 ቢሊዮን ፣ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለመደበኛ ወጪ ብር 316.9 ሚሊዮን ለካፒታል ወጪ ብር 10.0 ሚሊዮን በጠቅላላው ብር 326.9 ሚሊዮን ፣ ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት ለመደበኛ ወጪ 21.5 ሚሊዮን፣ ለፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ለመደበኛ ወጪ 28.1 ሚሊዮን ተደግፏል ። በድምሩ ለፌዴራል ፍ/ቤቶች ለመደበኛ ወጪ ብር 780.2 ሚሊዮን እና ለካፒታል ወጪ ብር 1.1 ቢሊዮን በአጠቃላይ ብር 1.9 ቢሊዮን ተደግፏል ።

4. የመ/ቤቱ ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች እና ግቦች

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 1 በ2015 የበጀት ዓመት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የመስጠት አቅምን ከሚቀርቡ መዛግብት አንጻር አሁን ካለበት 58% አፈጻጸም ወደ 80% አፈጻጸም ከፍ ማድረግ።	**ፕሮግራም1: የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት** የፌዴራል ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 25/88 በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት በተለያዩ ጉዳዮች ዓይነትና ደረጃ ለየፍ/ቤቶቹ በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ውሳኔ መስጠት፤እንዲሁም ተደራሽነታቸውን ማሳደግ፤	➢ የፍትሀዊ ውሳኔዎች አፈጻጸም፣ ➢ የፍርድ አፈጻጸምን ማረጋገጥ፣ ➢ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ፣ ➢ የተሻሻሉ የፍርድ ቤት አሰራሮች፣	➢ በመቶኛ ➢ በመቶኛ ➢ መቶኛ ➢ መቶኛ	80 97 97 80
ዓላማ 2 በ2015 በጀት ዓመት ለ31,100 የወንጀል፤ የፍትሐብሔርና የስራ ክርክር መዝገቦች እልባት መስጠት፤	**ፕሮግራም2: የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት** የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2013 ዓ/ም ተሻሽሎ በወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ሌሎች አዋጆች በተሰጠው ስልጣን መሠረት በተለያዩ ጉዳዮች ዓይነት በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ውሳኔ መስጠትና የተሰጣቸውንም ውሳኔዎች በማስፈፀም የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ፤	➢ እልባት ያገኙ 31,100 የዳኝነት መዛግብት ፣	➢ በመቶኛ	100

ስትራቴጂክ ዓላማዎች	የፕሮግራሞች/የንዑስ ፕሮግራሞች ስያሜና መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት		
		ውጤቶች	አመልካቾች	ግቦች
ዓላማ 3 በ2015 ዓ.ም ለ147,102 የወንጀል ፣የፍትሐብሔርና የስራ ክርክር መዝገቦች እልባት መስጠት	**ፕሮግራም 3፡የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት** የፌዴራል መጀመሪያደረጃ ፍርድ ቤት በተለያዩ ጉዳዮች ዓይነት በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ውሳኔ መስጠትና የሠጣቸውንምውሳኔዎችበማስፈጸም የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፤	➢ የተሰጡ ፍትሀዊ ውሳኔዎች	➢ በመቶኛ	98
ዓላማ 4 በ2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ፌ/ሸ/ፍ/ቤቶችን ውሣኔ የመስጠት አቅምን አሁን ካለበት 72.2% ወደ 90% አፈጻጸሙን ማሳደግ ።	**ፕሮግራም 4፡ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት** የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች በፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው ለሚመጡ የሙስሊሙ ህብረተሰብ በአዋጅ ቁጥር 188/1992 በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ለየፍ/ቤቶቹ የሚቀርቡትን የፍትሐብሔር ውሣኔዎችን በፈጣንና በቀልጣፋ መንገድ በግልጽነት ለተገልጋዩ መስጠት፡፡	➢ ለፍትሐ ብሔር ክርክሮች የተሰጡ ውሣኔዎች	➢ በመቶኛ	85
ዓላማ 5 በ2015 የምልመላ እና መረጣ ፣የጥቅማ ጥቅም ሽፋን፤ የዲስፕሊን ክስ አፈጻጸም አቅማችንን በማሳደግ የዳኝነት አካሉን ነጻነትና ተጠያቂነት ወደ 100% ማሳደግ	**ፕሮግራም 5፡የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ** በተሻሻለው የፌዴራል ዳኞችአስተዳደር ጉባኤ መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 684/2002 መሰረት የፌዴራል ፍ/ቤቶች ዳኞች ምልመላ ፣የዳኞችን ስነምግባር፣ የስራ አፈጻጸም ምዘና ፣የስራ ሁኔታ አወሳሰን በአጠቃላይ የተገልጋዮችን እርካታ ለማረጋገጥና የዳኝነት ነጻነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚሞክር ይሆናል ።	➢ ያደገ የተገልጋይ እርካታ	➢ በመቶኛ	100

5. የ2015 ለመ/ቤቱ ፕሮግራሞች የተደገፈ የካፒታልና የመደበኛ ወጪ

በሺህ ብር

የመ/ቤቱ/ የፕሮግራም መለያ ቁጥር	የፕሮግራሙ ስም	የካፒታል ወጪ					የመደበኛ ወጪ			ጠቅላላ ድምር
		ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ድምር	ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከመ/ቤት ገቢ	ድምር	
1	2	3	4	5	6	7=3+4+5+6	8	9	10=8+9	11=7+10
122	የፌዴራል ፍርድ ቤቶች	1,170,682.0				1,170,682.0	780,166.4		780,166.4	1,950,848.4
1	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	275,682.0				275,682.0	171,245.8	-	171,245.8	446,927.8
2	የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት	885,000.0				885,000.0	242,427.0	-	242,427.0	1,127,427.0
3	የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት	10,000.0				10,000.0	316,926.4	-	316,926.4	326,926.4
4	የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት	-				-	21,511.2	-	21,511.2	25,045.0
5	የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ	-				-	28,056.0	-	28,056.0	23,096.0

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት

1. የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫ

1.1 ተልዕኮ

በሀገራችን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገትና አስተማማኝ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማረጋገጥ፤ ማሳደግና መጠበቅ በመሆኑ ለተግባራዊነቱም ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ፤ የተሟላና ጥራት ያለው መረጃ በማዘጋጀት የአገራችንን ሠላምና ደህንነት ማረጋገጥ ::

1.2 ራዕይ

ለሀገራቱ ብሔራዊ ጥቅም የቆመ ጠንካራና ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ እና የተሟላ መረጃ በማዘጋጀት ብሔራዊ ደህንነታችንን የማረጋገጥ ሚና መጫወት::

2. ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር

የሀገሪቱ የ5 ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ እንዲሳካ ከአጋር መ/ቤቶች ጋር በመሆን የሀገራችን ፀጥታና ደህንነት አስተማማኝ እንዲሆን በማድረግ ለእቅዱ ማሳካት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው::

- ሕገ መንግሥታዊ ሥርአቱን የሚፈታተኑ ጥቃቶችን መከላከል፣
- አገርና ሕዝብን ከሽብርተኝነት መከላከልና ደህንነት ማረጋገጥ
- የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ከሚያናጉ ወንጀሎች መከላከል፣
- ከውጭ የመረጃና የስለላ ጥቃት አገሪቱን መጠበቅ፣
- መልካም አስተደደር እንዲሰፍንና የሕዝቡን ሰላማዊ ኑሮና እንቅስቃሴ የሚያውኩ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ግጭቶች መከላከል፣
